# አገር እንዴት ሰነበተች ቁጥር 42

ህዳር25ቀን 2015ዓም(04-12-2022)

ባለፈው የአገር እንዴት ሰነበተች ዘገባችን ያነሳነው በአብዛኛው በአገራችን ታሪክ በህዳር ወር ውስጥ የተከሰቱትን ጠቃሚና ጎጂ ክስተቶችን ነበር፤ አሁንም ህዳር ወር አልተገባደደም።ስለሆነም በዚሁ ህዳር ውስጥ የሆኑትንና የታዘብናቸውን አንስተን አስተያዬት የምንሰጥባቸው ይሆናል።በህዳር ወር ውስጥ ነበር ከዛሬ ሃያ ስምንት ዓመት በፊት አገራችንን ለመበታተን የሚያስችል አንቀጽ የተሸከመው የጥፋት ሰነድ ብለን የምንጠራው የይስሙላ "ሕገ-መንግሥት" መመሪያና ደንብ ሆኖ በጎሰኞች ስብስብ ጸድቆ እስከአሁን ድረስ ለዘለቀው የሰላም እጦት፣የአንድነት መናጋት፣ ለባሰ ደም መፋሰስ የተዳረግነው። አሁንም ይህ የጥፋት ሰነድ ከባለቤቶቹ ከጎሰኞቹ ስርዓት ጋር ካልተወገደ ያገራችን አንድነትና ህልውና፣ የሕዝቧም ሰላምና አብሮነት ሊረጋገጥ አይችልም።የአገርን ህልውናና ነጻነት ለማስጠበቅ የግድ አገር ወዳዶች የመሪነቱን ቦታ ሊይዙ ይገባል።በህዳር ወር ውስጥ ክፉና ደጉን ተቀብለን አስተናግደናል። ከተከናወኑት መካከል የብሔራዊ ኩራት ሆኖ በታሪክ መዝገብ ውስጥ ከሰፈረው መካከል አንዱን ብናነሳ የሚከተለውን ይመስላል።

አጼ ሚኒሊክ የውጭ አገር ንግድ ግንኙነትን ለማፋጠን ሲሉ የመጀመሪያውን የውጭ ገንዘብ ማር ትሬዛ( ጠገራ ወይም የድንጋይ ብር፣)በመባል የሚታወቀውን የአውትሪያ ንግሥት ማሪያ ትሬዛ የምትባለዋን ንግሥት ምስል የያዘ 250,000 ብር ገደማ አስመጥተው የመጀመሪያ የሆነውን ባንክ(ቁጭራ ባንክ)ተብሎ የሚጠራውን ከፍተው በአገልግሎት ላይ እንዲውል አደረጉ።ለጥቂት ዓመታት በጥቅም ላይ ውሎ ቀዳማዊ ሃይለሥላሴ ሥልጣኑን ከወሰዱ በኋላ ከኢትዮጵያ የወርቅ ክምችት ጋር በተያያዘውን ብሔራዊ ገንዘብ (ብር)እንዲተካና አገራችን ከውጭ አገር የከረንሲ ጥገኝነት እንድትላቀቅ ያደረጉት በወቅቱ የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስትር በነበሩት በአቶ መኮንን ሃ/ወልድ አስፈጻሚነት በዚሁ ህዳር ወር በአስራ ሶስተኛው ቀን 1939 ዓም ነበር።የኢትዮጵያ ብር በሌሎቹም አገሮች ተቀባይነት ኖሮት በንግድ ልውውጡ ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል።እንደ አሁኑ በሁሉም አቅጣጫ ሳንረክስና ሳንዋረድ ኢትዮጵያ ብሯም ፣ሕዝቧም የተከበረባት አገር ነበረች።የጎረቤት አገሮች በቅኝ ገዥዎቻቸው ፍራንክ ሲጠቀሙ ኢትዮጵያ የራሷን ገንዘብ አትማ ንግዷን ታካሂድ ነበር።ያም ለቀሩት ያፍሪካ ቅኝ ግዛት አገሮች ዓይናቸውን እንዲከፍቱ የበኩሉን ድርሻ ተጫውቷል።አሁን በ80ና ከዚያም በላይ በሆነ ብር የሚመነዘረው ዶላር በመጀመሪያው ወቅት ላይ መሳ ለመሳ የሆነ አቅም ነበረው፤ ከጊዜም በኋላ የዶላር አቅም እዬጎለበተ በመምጣቱ የዛሬ አርባና ሃምሳ ዓመት በኢትዮጵያ ውስጥ የነበረው ምንዛሬ ሁለት ብር ከሃያ ሳንቲም ብቻ ነበር።

አሁን ላለንበት ውርደት የዳረገን የራሳችን ድክመት መሆኑን ተረድተን ወደ ባሰ ደረጃ ይዞ ከሚያንደራድረን የቁልቁለት ጉዞ ለመውጣትና ወደ ነበርንበት ቦታ ለመመለስ የባርነት ቀንበር ካሸከመን የጎሰኞች ሥርዓት መላቀቅ ይኖርብናል።ያለፈው አኩሪ ታሪካችን እልህ ሊጭርብን ይገባል፣ አሁን የሰፈነው የውድቀት ጉዞ በአደንዛዦች በኩል የዕድገት ሂደት ነው ተብሎ የሚረጨውን ፕሮፓጋንዳ ልንቀበል አይገባም።የቀድሞውን ህዳር ክስተቶችን ከአለንበት ህዳር ወር ጋር ለመመዘን ይረዳን ዘንድ የተከሰቱትን ሁኔታዎች ለማቅረብ እንሞክራለን።

ላለፉት እረጅም ጊዜያት ሕዝቡን ወጥሮ የያዘው የኑሮ ውድነት እስከአሁን ድረስ መፍትሔ አላገኘም። የኑሮ ውድነቱ ብቻ ሳይሆን የሰላም እጦቱም የሕዝቡን ሰቆቃ አግዝፎታል።የፍትሕ እጦቱ ሕይወቱን መራራ አድርጎበታል። በተለያዩ የሙያ ዘርፍ የተሰማራ ሠራተኛ፣የተለያዩ የጎሳ ማንነት ያለው ማህበረሰብ፣የተለያዩ እምነት ተከታይ፣ተማሪው፣አስተማሪው፣አርሶ አደሩ፣ነጋዴው...ሁሉም በዪበኩሉ ስርዓቱ ያደረሰበትንና እያደረሰበትም ያለውን በደል በዪፈናው አምርሮ ሲቃወም ኖሯል፣አሁንም እየተቃወመ ይገኛል።ሆኖም ግን ተቃውሞው የተበታተነና በአንድ ግንባር ስር ያልተመራ በመሆኑ በተናጠል ከመጠቃት ውጭ ለሚፈልገው ግብ አላበቃውም።

አገር ጠል ብቻ ሳይሆን ኢሰብአዊነትን የተሸከሙ ሆዳቸው ሰፍቶ አይምሯቸው(ጭንቅላታቸው)የጠበበ ጎሰኞች ሥልጣኑን በጉልበት ነጥቀው በኢትዮጵያዊነት ላይ የሚፈጽሙት ግፍና ጭካኔ ተባብሶ ቀጥሏል።በተለይም በአማራው ማህበረሰብ ላይ ሁሉም የማርያም ጠላት ብሎ የተነሳበት ይመስላል። ሲጨፈጨፍ፣ሲፈናቀል፣ሲዘረፍ ከጎኑ የቆመለት ማህበረሰብ የለም።በግለሰብ ደረጃ ብቻ የመከራውን ጽዋ አብረው የተጎነጩ፣መጠቃቱን የሚኮንኑና ድምጽ የሆኑ ግን አልጠፉም።ለዚያ ታዲዎስ ታንቱና መሰሎቻቸው ምሳሌ ናቸው።በክልል በሚሉት ደረጃ ግን ለምን ብሎ የታገለ ሳይሆን የጠዪቀ የለም። ይባስ ብሎ በጸረ ኢትዮጵያዊነት ለተሰለፈው ጎራ ፊታውራሪ ሆኖ የሚያጠቃውና የሚያስጠቃው በአማራው ስም በክልል ደረጃ ሥልጣን የያዘው ቡድን ነው።

ብዙ መከራ መቀበሉ ሲመረው፣ ጥቃትና ግፉ ሲያንገሸግሸው ለመከላከል ሲነሳ ብርክ የለቀቀባቸው ቡድኖች ያለ የሌለ ሃይላቸውን አሰባስበው ዘመቻ ከፍተውበታል።ያንን ዘመቻ ለመቋቋም ጥረት ቢደረግም በቂ አልሆነም።በፋኖ ደረጃ የተቋቋመው አገር ወዳድ ሕዝባዊ ሠራዊት እራሱን ከሥርዓቱ ብብት ሙሉ ለሙሉ ማላቀቅ አልቻለም።ባለፈው ጊዜ የአንድነት መግለጭ መውጣቱን ደግፈን ነበር ፤ አሁንም እንደግፋለን።ሆኖም ግን የአንድነት ግንባሩ ትግል ግቡን እንዲመታ ጠላትና ወዳጁን በቅጡ ለይቶ እንዲቆም፣ያለበትን ውዥንብር እንዲገፍ ማሳሰብ እንወዳለን።የሚያሳድደውን የክልሉን መንግሥት እንደ አጋር በማዪት የይደረግልኝ ደጅ ጥናት ወይም አቤቱታ ማቅረብ ስህተት መሆኑን ለማሳወቅ እንወዳለን።የክልሉ አስተዳደር የሥርዓቱ አንዱ ክንፍ ስለሆነ መወገድ ያለበት እንጂ እንደ ወገን መቆጠር የለበትም እንላለን። ፋኖን የሚያሳድደው፣ከ15 ሺህ በላይ ያሰረው ማን ሆነና? በአማራው ማህበረሰብ ላይ ለደረሰው ሁሉ የመጀመሪያ ተጠያቂው ብአዴን በሚል ስም የክልሉን ሥልጣን የጨበጠው ባንዳ ቡድን ነው።ጽዳቱ ከቤት መጀመር አለበት።"ጠላትማ ምን ጊዜም ጠላት ነው፣ አስቀድሞ መምታት አጎብዳቢውን ነው" የተባለውም ለዚያ ነው።ይህ በተግባር መገለጽ አለበት።ፋኖነት ጎፈሬ አበጥሮ በከተማ መሃል ማውደልደል ወይም ከጠላት ጋር መደራደር አይደለም።በፋኖነት ላገራቸው ተጋድሎ ያደረጉት አባት አያቶቻችን ከጣሊያን ጋር በአፈሙዝ ተነጋገሩ እንጂ፣ለጥ ብለው እጅ በመንሳት የይግባኝና የልመና ደብዳቤ አላቀረቡም።ፋኖ በጫካ መሽጎ በሽምቅ ውጊያ ዘራፍ! ይላል እንጂ በዪሆቴል አዳራሹ እሰጥ አገባ፣ወይም እሽሽ ገዳሜ አይልም።

በዱር በገደል ብዙ መስዋእት የከፈሉና በመክፈልም ላይ ያሉ ጀግና ፋኖዎች እንዳሉ ሁሉ፣እነሱን ለማጥፋት የተሰለፈ በፋኖ ስም በአገር አጥፊው በባእዴን በኩል የተደራጀ ቡድን መኖሩ በስፋት ይነገራል።ይህንን አውቆና አረጋግጦ በነዚያ ላይ እርምጃ መውሰድ እራስን ከአደጋ መከላከል ብቻም ሳይሆን ለትግሉም ጥራትና አስተማማኝ ስለሆነ ችላ መባል የለበትም።አሳ ግማቱ ከጭንቅላቱ ነውና የቅጣት እርምጃው በሙስናና በሌብነት ብሎም በባንዳነት ከተጨማለቀው ከብአዴን ስብስብ ይጀምራል።

ይኸው ምንደኛ የክልሉ አመራር በሰሞኑ ዓመታዊ ስብሰባ ማካሄዱ ተሰምቷል።በዚህ ስብሰባ ላይ በአገራችን በተለይም በአማራው ላይ የደረሰው ችግርና አደጋ በአጀንዳ ቀርቦ ስህተቶችን በማመን

ይታረማሉ ብሎ የጠበቀ ቁጥሩ ቀላል አልነበረም፤እኛ ግን የብአዴንን ማንነት ስለምናውቀውና ስለምንረዳ የዚህ አይነት ውዥንብር የለብንም። የክልሉን ሕገመንግሥት ለማሻሻል ፍላጎትና ድፍረት ከሌለው ምንደኛ የምንጠብቀው አይደለም።የክልሉም ሆነ አገር አቀፉ ሕገመንግሥት ተብዬው የጥፋት ሰነድ ተቀዳዶ መጣልና በእውነተኛ ሕዝብ በተሳተፈበት፤አምኖ በተቀበለውና በአጸደቀው፣ከመንግሥት በላይ በሆነ ሕገ መንግሥት መለወጥ አለበት የሚለው የማይፋቅ የማይለወጥ አቋማችን ነው።ለዚያም እንታገላለን። በእንቁጣጣሽ ሰሞን የደነቀረ አበባዬ ሆይ! እንዳለ ይሞታል ሆነና ያንኑ የጥፋት ሰነድ ለሕዝቡ ሰላምና አብሮነት፣ላገራችንም አንድነት የጠቀመ ነው በሚለው ተስማምተው ተበተኑ።ለዚያም ነው ከእባብ እንቁላል እርግብ አይፈለፈልም፣ከብአዴን ስብስብም መልካም ነገር አይፈልቅም የምንለው። እባብ በእንጭቹ እንደሚባለው ፣ብአዴንም ከምንጩ መድረቅ አለበት እንላለን።

ይኸው ጉደኛ ብአዴን አማራውን መታደግ ሲገባው ለአማራው ጨፍጫፊ ለኦነግ ብልጽግና አሽባሪ ቡድን የገንዘብ ተፋሰስ በማድረግ ማጠናከሩን ሾልኮ በወጣው መረጃ ለማወቅ ችለናል።ያሰማራቸው የዜና ዘጋቢዎቹ ጋዜጠኛ፣ቀራጭ(የካሜራ ሰው)እና እረዳቱ በኦነግ ታግተው የጠዬቁትን 3 ሚሊዮን ብር ሳያቅማማ መክፈሉ ተሰምቷል። እባካችሁ ልጨምርላችሁ ብሎ ከተጠዬቀው በላይ ለመክፈል ይደራደር ይሆን እንጂ እምቢ ብሎ ይግደረደራል የሚል እምነት የለንም።

ከብአዴን መንበረ ሥልጣን የተወገዱት እነ ገዱ አንዳርጋቸው፣ዩሃንስ ቧያለው በመወገድ ጠርዝ ላይ ያለው ደመቀ መኮንንና ሌሎቹ በአማራው ስም ሌላ ድርጅት ለማቋቋም በመንደፋደፍ ላይ መሆናቸውን ጭምጭምታ ሰምተናል።ይህ አማራውን የመናቅ ትልቅ ድፍረት ሆኖ አገኝተነዋል። ሕዝቡን ደደብና አስተዋይነት የጎደለው፣እንደ ከብት የሚነዳ አድርጎ ከመቁጠር የተነሳ እብሪት የወለደው አስተሳሰብ ከመሆኑም በተጨማሪ ለ32 ዓመታት ለፈጸሙት ጥፋት ከሚጠብቃቸው የሕዝብ ፍርድ ለማምለጥ በጥቅም ገዝተን ወይም በጎጥ ህሳቤ ጠፍንገን ከጎናችን እናሰልፈዋለን የሚሉት ደካማ መኖሩን በመተማመን ይሆናል።ባንዳነት ዳግም እንዳያንሰራራ ለማድረግ በነዚህ ላይ የማያዳግም እርምጃ መውሰድ ተገቢ ነው።አማራው ማህበረሰብ ለመብቱ የሚቆሙለት የሃቀኛ ታጋዮች ድሃ አይደለም። ብዙዎች ህይወታቸው ሳይቀር ከፍለውለታል፣ብዙዎችም የተፈለገውን መስዋእትነት ለመክፈል ዝግጁ ናቸው።የቀረው ሁሉንም የሚያሰባስብ ድርጅት አለመኖሩ ብቻ ነው።የአጥፊዎቹ ጎራ ከመንግሥታዊ መዋቅር ጀምሮ የሚቆጣጠሩበት ድርጅት አላቸው።

ከላይ እንደገለጽነው ያልተነካ ፣ጥቃት ያልደረሰበት የህብረተሰብ ክፍል የለም።ሁሉም በዬፊናው ይጮሃል፤የፍትሕ ያለህ ይላል።ጩኸቱን ተቀብሎ የሚያስተጋባበት የጋራ ልሳን ግን የለውም።የአንዱ ጉዳት የኔም ነው ብሎ የሚቆምበት የትብብር መድረክ አልተፈጠረም፤ለመፍጠር የተደረገውም ሙከራ በመጠላለፍ ሴራ ተሰናክሎ ቀርቷል።አሁንም የአገር አቀፍ የትብብር መድረክ(National Solidarity Forume) መፈጠር አለበት።የዬካቲቱ የትግል አንድነት መርሆ መደገም አለበት።እስላሙና ክርስቲያኑ፣ ተማሪውና አስተማሪው፣የፋብሪካ ሠራተኛውና አርሶ አደሩ፣የሲቪል ተቋማት ሠራተኛውና መለዮ ለባሹ(ወታደሩ) ድርጅት ሳይኖረው ተናቦ ባደረገው ትግል ምንም እንኳን ውጤቱ ከድጡ ወደማጡ ወይም ከምጣዱ ወደ እሳቱ ቢሆንበትም የነበረውን ባላባታዊ ሥርዓት ለማሶገድ የቻለው በትግል አጋርነት ነበር።ጎሳና ሃይማኖት ሳይለዬው ሁሉም ለአገሩ መሻሻል፣እድገት፣ ለሰብአዊ መብትና ለፍትሕ ቆሞ ብዙ መስዋእት ከፍሏል።ከ50 ዓመት በፊት ዴሞክራሲ ብሎ ቢጮህም ለዲሞክራሲ ሳይበቃ ጥያቄው ለሁለት ትውልድ ተርፏል። አሁንም ችግሩ የባሰ እንጂ ያነሰ አይደለምና ይበልጥ በአንድነት ቆሞ መታገልን ይጠይቃል።ለዚያ ካልበቃ ችግሩ የትውልድ ውርስ ሆኖ ይቀራል።ለስር ነቀል ለውጥ እና ለዴሞክራሲ ስርዓት እንዲበቃ ድርጅታዊ መልክ በያዘ መልኩ የዬካቲቱ የጋራ ትግል መንፈስ ይመለስ እንላለን።

በሰሞኑ ብቻ የሚካሄደውና የሚሰማው የሕዝብ እሮሮ ለዚያ ድርጅታዊ ትግል በር መክፈቻ ይሆናል። የመምህራኑ የደሞዝ ጭማሪ ጥያቄን ተከትሎ የተወሰደው የመንግሥት የበቀል እርምጃ ሁሉንም የማህበረሰብ ክፍል የሚቀሰቅስ ደወል ነው፣ከዩኒቨርሲቲ መምህራን ውስጥ ከ30% በላይ ያም ከ12 ሺህ ያላነሱ መምህራንን ከሥራ ገበታቸው ለማሰገድ መታቀዱ በትምህርት ደረጃና ጥራቱ ላይ የተከፈተ ዘመቻ ብቻ ሳይሆን ትውልድን የሚገድል፣አገርን የዕውቀት መካን የሚያደርግ ሴራ ነው።ይህንን ዕቅድ ተግባራዊ ለማድረግ ልማደኛው የመምህራን ጸር የሆነው ብርሃኑ ነጋ ባለው የትምህርት ሚኒስትርነት ስልጣን ለምክር ቤት ተብዬው አቅርቦ ለማስፈጸም ፈቃድ ጠይቋል። በዚህ ቁጥር ልክ ስር የሚተዳደረው ቤተሰብ ሲደመርበት ለችግር የሚጋለጠው ዜጋ ቁጥሩ በትንሹ ከ60 ሺህ በላይ እንደሚሆን ጥርጥር የለውም። የመምህራኑ አድማ በነገው እለት በህዳር 26 ቀን የታሰበ ሲሆን ያንን ለማደናቀፍ መሪዎች ናቸው የሚባሉትን ሁሉ ለቃቅሞ ለማሰር አሰሳው ከጀመረ ውሎ አድሯል።አብይ አህመድም በግላጭ የመጨረሻ እርምጃ እወስዳለሁ ሲል ዝቷል።አድማው ይሳካ አይሳካ የሚታወቀው ቀኑ ሲደርስ ነው።

ከትምህርት ዘርፍ ሳንወጣ ሌላው ደግሞ በተማሪዎች የተካሄደው እምቢ ባይነት ነው።በሸሮሜዳ አካባቢ በሚገኙት ትምህርት ቤቶች በተለይም በአምሐ ደስታ ት/ቤት በህዳር 22 ቀን የኦነግን ባንዲራ እንዲሰቅሉና የኦነግን መዝሙር እንዲዘምሩ የተገደዱት ተማሪዎች እምቢ አሻፈረን በማለት ተቃውሟቸውን ገልጸዋል።የኦነግን ባንዲራ ቀዳደው የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ከፍ አድርገው በመያዝ “ይኸ ነው ባንዲራው” እያሉ ሲዘምሩ ከፖሊስና በትምህርት ቤቶቹ ውስጥ በተሰገሰጉ ካድሬ መምህራን ድብደባና እንግልት ደርሶባቸዋል፤ቁጥራቸው ቀላል ያልሆኑ ተማሪዎች ቆስለውና በፖሊስ ታፍነው መወሰዳቸው ታውቋል። በማግስቱ በህዳር 23 ቀን በጉለሌ ክ/ከተማ በሚገኙት ድል በትግልና አዲስ ተስፋ በተባሉት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በተመሳሳይ ምክንያት ተማሪዎች፤ አስተማሪዎችና ወላጆች የተሳተፉበት ተቃውሞ ተቀስቅሶ ከፖሊስና ከጸጥታ ሃይሎች ጋር በተደረገው ግብ ግብ ብዙ ተማሪዎች ቆስለዋል። ብዙዎችም ታፍነው ተወስደዋል። ይህ አይነቱ የተማሪ እንቅስቃሴ ሲደረግ የመጀመሪያ አይደለም።ከዚህ ቀደም ሲልም በአዬር ጤና፣በጨርቆስና በመድሃኔ ዓለም፣ በመርካቶ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተመሳሳይ ተቃውሞ ተካሂዷል።ችግሩ የተማሪውን እንቅስቃሴ የሚያስተባብርና ከመምህራኑ፣ከአርሶ አደሩ፣ከሃኪሞች፣ከነጋዴዎች፣ከተፈናቃዮች፣ከፋኖዎች ጋር የተቀናጀ አገር አቀፍ እንቅስቃሴ የሚመራ ድርጅት አለመኖሩ ነው። በዛሬውም ዕለት በህዳር 25 ቀን 2015 ዓም በእንጦጦ በቀድሞው አምሃ ደስታ ት/ቤት የመንግሥት አካል ወላጆችንና ተማሪዎችን ለማነጋገር በጠራው ስብሰባ ላይ ተቃውሞ ተቀስቅሶ ስብሰባው ሳይሳካ ቀርቷል።ወላጆችና ተማሪዎቹ መንገድ ላይ ወጥተው ፣የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ከፍ አድርገው ይኸ ነው ባንዲራው፣ እናት ኢትዮጵያ የደፈረሽ ይውደም!በሚለው ወኔ ቀስቃሽ መዝሙር የታጀበ ትልቅ ተቃውሞ አሰምተዋል። እኛም ይበል ብለናል፥ሌላው የአዲስ አበባ ሕዝብ ከፍርሃትና ከባዶ ተስፋ ድባብ ወጥቶ ንቅናቄውን እንዲቀላቀል፣ለአገር አቀፉ እምቢተኝነት ፋና ወጊ እንዲሆን ጥሪ እናደርጋለን።

በያቅጣጫው ቦግ እልም የሚለው የተቃውሞ ነበልባል ስጋት የለቀቀበት የተረኛው አገዛዝ የሚይዝ የሚጨብጠውን አጥቶ በራሱ ውስጥ ሳይቀር ትርምስምስ ውስጥ ገብቶ እዬተባላ ነው።ሌባና ሙሰኛ በሚል ስያሜ እያጭበረበረ የጠፍ ዶሮ እዬፈለገ ጥቂቶችን መስዋእት ለማድረግ በመሞከር ላይ ነው። ሕዝቡም ትልቁ አሣ ትንሹን አሳ እያሳደደው ነው በማለት አላግጦበታል።ኢሕአዴግም ሆነ ብልጽግና የተዋቀሩበት ተክለሰውነታቸው(Anatomy) ቢመረመር ሙስና፣ሌብነት፣ዘረፋ፣ውሸት፣ጎሰኝነት፣ ኢሰብአዊነት፣ክህደት፣ጨካኝነት፣ባንዳነት ከሚባሉ ህዋሳት ለመሆናቸው በተግባራቸው በገሃድ ፈጦ ይታያል። የደም ሥራቸው የሚረጨው እነዚህን ከይሲ ምግባሮች ነው።ከነዚህ ቅን ልቦና ከሌላቸው

አረመኔዎች መልካም ነገር አይጠበቅም።መፍትሔው እነዚህን የሰው አረሞች መንጥሮ በመልካም ሰዎች፣በአገር ወዳዶች፣ለሰብአዊ ፍጡር ቀርቶ ለእንስሳት በሚራሩ ሰውነትን በተላበሱ መተካት ነው።

የኦሮሞ ክልል በሚባለው የደም መሬት በሆነው በወለጋ ውስጥ የሚፈጸመው የአማራ ማጽዳት ጭፍጨፋ በተቀናጀ መልኩ ቀጥሏል።ከኦነግ አሸባሪ ቡድን ጋር ተባብሮ በክልሉ መንግሥት የሰለጠነውና የታጠቀው ልዩ ሃይል የጥቃቱ ፈጻሚ ሆኗል።ከመከላከያውም የጎሳ ማንነታቸው የሳባቸው እጃቸውን በመስጠትና መረጃ በማቀበል ተባባሪ ሆነዋል።ለተጨማሪ የመሣሪያ ግባት ምንጭ ሆነዋል። አባ ገዳ የተባለውም የኦነግ ነፍስ አባት ለጨፍጫፊዎቹ አማላጅ ሆኖ ቀረበ እንጂ ለሚጨፈጨፉት ዜጎች ድምጹን አላሰማም።

በሰሜኑም በኩል ወያኔ ጉልበቱን እያጠናከረ በመሄድ ላይ ነው።ለይምሰል የሰላም ድርድሩን ውሳኔ አከብራለሁ ይበል እንጂ ምክንያቶች እዬፈለገ የተምታታ መግለጫ በማውጣት ላይ ተሰማርቷል። ሕገመንግሥቱ እንዲከበር ለማድረግ ጦርነት ገጥመናል፣እንደሚከበር ስናረጋግጥ ደግሞ ጦርነቱን አቁመናል።ካልተረጋገጠ ደግሞ ከጦርነት የሚያቆመን የለም ብሏል።ሕገ መንግሥቱ ይከበር ሲሉ የወልቃይትና ጠገሌ፣የራያና አዘቦ ለም መሬት በሕዝበ ውሳኔ በእጃችን ይገባል ከዚያም አንቀጽ 39ኝን ተጠቅመን እንገነጠላለን ከሚለው ድብቅ ዓላማቸው በመነሳት ነው።ምንም aneኳን የአብይ አህመድ መንግሥት ከዚህ ሴራ የተለዬ አቋም ባይኖረውም በቀላሉ አማራውን ለማንበርከክ የሚቻል አይሆንም።የሱዳን ጦር የያዘውን መሬት ማስለቀቅ ተስኖት እደራደራለሁ ከሚል መንግሥት በፈጠሩትና የዓላማ አጋር በሆኑት ወያኔዎቹ ላይ የሚጨክን አንጀት ይኖ,ዋል ብሎ ማሰብ ጅልነት ነው።እራስ ምታት የሆነበት በትግራይ ውስጥ የሰፈረው የኤርትራ ወታደር ብቻ ነው።ኢሳያስ አፈወርቂ አስተማማኝ ዋስትና ወይም ጥቅም ካላገኘ በስተቀር በቀላሉ የሚለቅ አይመስልም።ካለቀቀ ደግሞ የምዕራባውያንና በተለይም የአሜሪካኖቹ አርጩሜ የሚያርፈው በአብይ አህመድ መዳፍ ሥር በወደቀችው አገራችንና ሕዝቧ ላይ ነው።የአብይ አህመድ ምርጫ ምን እንደሚሆን የምናዬው ይሆናል።

የፖለቲካውንና የኤኮኖሚውን ቀውስ እንዲሁም የአማራውን ማህበረሰብ መነሳሳት ተከትሎ የፖለቲካ ድርጅቶችንም የአቋም መንሸራተት እያመሳቸው ነው።ከሁሉም በላይ በልማደኛው የግንቦት ሰባት ውስጥ የሚታዬው የማደናገር ሙከራ አይተነው ጊዜ ወደሚያደላው የሚል አድርባይነትን ያንጸባረቀ ሆኖ አገኝተነዋል።በአንዳርጋቸው ጽጌ በኩል የተነዛው የብልጣብልጦች የፖለቲካ ጨዋታ ለማያውቅሽ ታጠኝ የተባለውን ምሳሌ እንድናስታውሰው አድርጎናል።ከዚያም ባለፈ

በምን አወቅሽበት በመመላለሱ፣

ሲከፋሽ ወደ እኔ ሲደላሽ ወደ እሱ።

የሚለውን ዘፈን እንዲያዳምጡት በአክብሮት እንጋብዛቸዋለን።ለነሱና ለመሰሎቻቸው የኢትዮጵያ ሕዝብ ደጋግሞ በግም ውሃ ውስጥ የሚታጠብ ሞኝ አይደለም እንላቸዋለን።ለጎሰኞቹ ስርዓት መከታና ጠበቃ ሆነው ለደረሰው ቀውስ ሁሉ ከሚጠዬቁት የፖለቲካ ድርጅቶች አንዱና ዋናው ግንቦት ሰባት መሆኑን ልናረጋግጥላቸው እንወዳለን። ለማንኛውም ባለቤቱን ካልናቁ አጥሩን አይነቀንቁ ይባላልና የኢትዮጵያ ሕዝብ በተለይም አማራው በነዚህ አስመሳዮች ሳይታለል ለክብሩና ለመብቱ በጋራ መቆም አለበት።ያለፈ ሥራቸውን መመዘኛ አድርጎ ሊጠቀምበት ይገባል።ጋዜጠኛው ሲታሰር፣ወጣቱ ሲታፈን፣ ፋኖ ሲሳደድ፣ዜጋ ሲፈናቀል እያዩና እዬሰሙ ለተቀመጡበት ወንበርና ለሚያገኙት ጥቅም ሲሉ ድምጻቸውን አጥፍተው ቆይተዋል።መሪያቸው ብርሃኑ ነጋም 12 ሽህ የዩኒቨርሲቲ መምህራን አባርራለሁ ብሎ ሲነሳ የፓርቲው አባላትና ደጋፊዎች ለምን ብለው አልጠየቁም።

በመጨረሻ ላይ ልናነሳ የምንወደው ለብዙ ስቃይና መከራ ተዳርጎ የነበረው ጋዜጠኛ ታምራት ነገራ ምንም እንኳን መሰደድን ባንመርጥም ህይወቱን ለማዳን ከነባለቤቱ በሰላም በመውጣቱ እንኳን ለዚህ አበቃህ ለማለት እንወዳለን።በአገር ቤት ሆኖ ለመንቀሳቀስ የተነፈገውን መብቱን በውጭ አገር አግኝቶ ትግሉን እንደሚቀጥል ተስፋ እናደርጋለን፤ መጀመሩንም በጥቂቱም ቢሆን ታዝበናል።ባይቀጥልበትም የሚችለውን ያህል አድርጓልና አይወቀስም።አሁን ቅድሚያ የተጎዳ መንፈሱን በማደስና በመጠገን ላይ ቢሆን የበለጠ ሊጠቅም ይችላል።አፍርሶት የሄደውን ኑሮ ለመመለስ ጊዜ ይጠይቃልና ብርታቱን ይስጥህ እንለዋለን፤በአካባቢው ያሉትንም አገር ወዳዶች ከጎኑ እንዲቆሙ ጥሪ እናደርጋለን።

ሌላው በመከራ ውስጥ የሚኖረው የኢትዮጵያ ተሚጋች አንጋፋው የብዕር ታጋይ አቶ ታዴዎስ ታንቱ እንዲፈታና ከቤተሰቡ ጋር እንዲቀላቀል ሁሉም አገር ወዳድ ድምጹን እንዲያሰማለት ፣ለችግር የተጋለጡትንም ቤተሰቦቹን፣ሚስቱና ልጆቹን ለመርዳት ሁሉም እንዲረባረብ ጥሪ እናደርጋለን።

የተቀጣጠለው ሕዝባዊ ትግል ይፋፋም!ሕዝባዊ ግንባር ይጠንክር

የጎሰኞች ስብስብ ያሰፈነው ሥርዓት ይወገድ!!

ኢትዮጵያ አገራችን በአንድነትና በነጻነት ለዘለዓለም ትኑር!!!